## ደንብ ቁጥር-------------------/2004

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልላዊ መንግስት የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ለማቋቋም የወጣ ደንብ

በክልሉ የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ አጠቃቀምን አስመልክቶ ህብረተሰቡ የንጹህ ወሃ፤በቂና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ወጥነት ያለውና ጠንካራ አሰራር ያልነበረው መሆኑን በመገንዘብ፤

ንጹህ ውሃን መጠቀም የዜጎች መብት በመሆኑና ይህን መብት ተጠያቂነትና ሃላፊነት በተሞላ አግባብ የባለቤትነት ስሜት ለመፍጠር የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማጎልበት የንጹህ ውሃ ተጠቃሚነት ከምንጊዜውም በበለጠ ማረጋገጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገጠር የቤት ውስጥ ውሃ አጠቃቀምን አስመልክቶ ከዚህ በፊት በዘርፉ ሲከሰቱ የነበሩትን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመቅረፍ፤የውሃ ተጠቃሚዎችን በማህበራት በየደረጃው በማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን በመወሰን ረገድ የክልሉ መንግስት በርካታ ተግባራትን እየፈጸመ በመሆኑና ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ለማደራጀትና ለማቋቋም በአዋጅ ቁጥር 71/2000 የደነገገ በመሆኑና ለአተገባበሩም የማስፈጸሚያ ደንብ በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 59(1) እና በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 36 መሰረት ይህ ደንብ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

### 1.<u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የቤኒሻንገል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ሊቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር----------/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1. " ሐብቶች " ማለት ፣ የዉሃ አቅርቦት ተቋሙን አካላት ጨምሮ፣ ማንኛዉን የማህበር ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብርት ወይም የተጠራቀመ ጥሬ ገንዘብ ማለት ነዉ ፡፡

2. “ ማህበር” ማለት በአዋጅ ቁጥር 71/2000 እና በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመና የተመዘገበ የገጠር የቤት ዉስጥ አገልግሎት ዉሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ማለት ነዉ ፡፡
3. “ ተቆጣጣሪ አካል ” ማለት የክልሉ የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ ወይም በዚሁ ቢሮ የተወከሉ መምሪያዎች ፣ ጽ/ቤቶች ወይም ዴስኮች ናቸዉ፡፡
4. “ጠቅላላ ስብሰባ” ማለት የማክበሩ አባላት ስብሰባ ማለት ነው ፡፡
5. “አባል” ማለት የማህበረሰባዊው አካል የሆነና የማህበሩ የሚጠይቀውን መመዘኛ በመከተል በሙሉ አባልነት የተመዘገበ ወይም በልዩ ሁኔታ የማኅበሩ አባል እንዲሆን የተወሰነለት ሰው ማለት ነው ፡፡
6. “ሰው” ማለት ማንኛውም ተፈጥሯዊ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያገኘ ማለት ነው ፡፡
7. “የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ አቀርቦት” ማለት የታቀደበት ዋና ዓላማ ለገጠር ኗሪዎች የቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል ውሃ የማቅረብ ሥራ ማለት ነው ፡፡
8. “የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ” ማለት ለመጠጥ ፣እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደ ውሃው መብቃት፣ ለማጠብና ለመተጣጠብ፣ ለቤት ውስጥ እንስሳትና ለጓሮ አትክልት የሚውል ውሃ ማለት ነው ፡፡
9. “ የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ አቀርቦት ተቋም” ማለት እነደ አግባብነቱ የአቅርቦቱን መዋቅሮች፣ ማከማቻዎች፣ ካናሎች፣ ውሃ መሳቢያዎች፣ ኤሌክትሪክ ማመንጫዎች፣ የማከፋፈያ መስመሮችን ጨምሮ እንዲሁም ማንኛውም ሌላ ውሃ ለመቅዳት ( ለመውሰድ) እና ለተጠቃሚዎች ለማከፋፈል ግልጋሎት ላይ የሚውሉ መሳሪያዎችን የሚያጠቃልል ነው ፡፡
10. “ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ” ማለት የየማኅበራቱ ስራ አስፈጻሚ አካላት ሆኖ የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃን በመመለከት ለአባላቱ ዕቅድ ማውጣትን ፣ማስፈፀምን፣ ኦፕሬሽንን ፣ጥገናን፣ ማስፋፋትና እንዲሁም ሌሎች የማህበሩን ጉዳዮች ለማከናወን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠና በአዋጅ ቁጥር 71/2000 እና ከዚህ በኋላ ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ በመባል የሚጠራ ነው፡፡
11. “ ክልል ማለት” የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ማለት ነው፡፡
12. “ ቅድመ መቋቋም ተግባር” ማለት ማኅበሩ ከመቋቋሙ በፊት ለቅድመ ዝግጅት ማለትም ህገ ማህበርና ሌሎች የውስጥ አሰራሮችን በማዘጋጀትም ሆነ በማዳበር በተጠቃሚው ማህበረሰብ እንዲጸድቅና ማኅበሩ እንዲመሰረት በማድረግ የማህበሩን ምዝገባ የማጠናቀቅ ሥራ ማለት ነው ፡፡
13. “ የመጀመሪያ ደረጃ ማህበራት” ማለት ሁሉም አባላት የሚገኙበት ጠቃላላ ጉባኤ እና በቀጥታ የተመረጠ ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ/ቦርድ

የሚገኝበትና ሁሉም ተጠቃሚ የማህበረሰብ አባላት የማህበሩ ከፍተኛ ወሳኝ አካል የሆነው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት በመሆን የሚመሰርቱት አንድ ነጠላ ማኀበር ማለት ነው ፡፡

14.“ የሁለተኛ ደረጃ ማኀበር” ማለት በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 27 መሰረት ከሁለት በላይ ወይም በርካታ የመጀመሪያ ደረጃ ማህበራት ለተለያየ የሥራ ብቃትና ቅልጥፍና ሲሉ በቀበሌ ወይም በወረዳ ደረጃ በፈቃደኝነት አንድ ላይ በመሆን የሚያቋቁሙት ልዕል ማህበራት ዓይነት ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በክልሉ ውስጥ በሚገኝ የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ አቀርቦት ማኀበራት፣ ተቋም እና ተጠቃሚዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡

# ክፍል ሁለት

# የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎቸ ማህበራት አደረጃጀትና አቋቋም ሂደት

## 4. የግንዛቤና የማግባባት ተግባራት

የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎቾ ማኀበራት በተቻለ መጠን ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በማቀፍ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ ስለሚኖርባቸው ማኀበሮች ከመመስረታቸው በፊት ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት የቅድመ ዝግጅት ስራዎች መስራት አለባቸው፡፡

1. የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎችን ማህበራትን ለማቋቋምና ለማደራጀት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በቅድሚያ ስለገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃና ስነ ንጽህና ከጤና አንጻር ስላለው ማኀበራዊ ጠቀሜታ እና እንዲሁም በማኅበር የመደራጀትን የውሃ ተቋማትን ፣ የማጠናከሪያና የጥገና ወጭዎች ሙሉ በሙሉ

መሸፈንና ቀጣይነት ባለው መልኩ የውሃ ተጠቃሚ ለመሆን በማህበራት የመደራጀትን ጉልህ ጠቀሜታ ዙሪያ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ህብረሰተሰቡን የማሳመን ተግባር ይከናወናል፡፡

2. ከለይ በንዑስ ርዕስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገውን ተግባር በመከተል ተጠቃሚውን ህብረተሰብ ለቅድመ አደረጃጀት እንዲያመች የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ቅድሚያቸው መሆኑን ማረጋገጥ ፡፡
3. ከሚመለከተው የወረዳ/የቀበሌ አመራር፣ የውሃ ጽህፈት ቤት ባልደረቦች ጋር በመሆን የቅድመ ማቋቋም ተግባር የሚያመቻቹ ከሦስት ያላነሱና ከሰባት ያልበለጡ ጊዚያዊ ኮሚቴ ማቋቋም እና ኮሚቴውም በዚህ ደንብ የተጣለበትን ኃላፊነት እንዲወጣ ማድረግ፡፡

## 5. የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች ማኀበራት የማቋቋምና ህጋዊ ሰውነት እንዲኖረው ስለማድረግ

ከላይ በአንቀጽ 5(4) ሥር የሚቋቋመው ኮሚቴ፤

1. ከሚመለከተው የወረዳ ውሃ ጽ/ቤት ጋር በመሆን ማኀበሩን ለማቋቋም የሚያስችል ህገ ማህበር፤ የማህበሩን አባላት ምዝገባ የማጠናቀቅ ተግባር ይፈጸማል ፡፡
2. የተጠናቀቀውን የቅድመ ምስረታ ተግባራትን ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በማቅረብና በማወያየት እንዲጎለብት ማድረግ፤
3. ተቀባይነት ባገኘው የቅድመ ምስረታ ተግባር መሰረት በህብረተሰቡ አማካኝት ማህበሩ እንዲቋቋም ማድረግ ፤
4. ማህበሩ ከተደራጀና ከተቋቋመ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 7 መሰረት የማህበሩ ምዝገባ እንዲጠናቀቅ በማድረግ ለተቆጣጣሪው አካል በማቅረብ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ በማድረግ የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ማድረግ፤
5. ማህበሩን የማቋቋም ስራ ሲጠናቀቅ ማህበሩን ለመምራት በአዋጅ ቁጥር 71/2000 እና በዚህ ደንብ ለተገለጹት አካላት ስራውን ማስረከብ ፤

6. በቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበርነት የመደራጀቱ ህጋዊ አስፈላጊነት ምን ጊዜም እንደተከበረ መቆየት ያለበት ሲሆን በማንኛውም ጊዜ የማህበሩ አባል የመሆን መብትም የተከበረ ይሆናል፡፡

## 6.የምደባ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ታሳቢ መሆን ያለባቸው ጉዳዮች

የውሃ ተጠቃሚዎችን ከውሃ ተቋሙ የአገልግሎት አቅም ጋር ለማመጣጠን የሚከተሉትን ነጥቦች ማዕከል በማድረግ የተጠቃሚዎች ድልደላና ምደባ ይካሄዳል፡፡

1. የተጠቃሚዎቹ ብዛት ከውሃ ተቋሙ በሚገኘው ውሃ በሙሉ ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑንና አለመሆኑን መለየት፤
2. ከተጠቃሚዎቹ ወይም ይጠቀማሉ ተብለው በዕቅድ ከተያዙት ተገልጋዮች የሚሰበሰበው የውሃ ክፍያ የሥራ ማስኬጅያና የጥገና ወጭዎችን ለመሸፈን መቻሉን ታሳቢ ማድረግ ወይም እነዚህን ወጭዎች ለመሸፈን ተጠቃሚዎቹ ክፍያቸውን ከፍ ለማድረግ ፍቃደኞችና ችሎታውም ያላቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ፤
3. የራሳቸው የውሃ አቅርቦት ለሌላቸው አጎራባች ማህበራት የውሃ አገልግሎት ለመስጠትና ለዘላቂነታቸው አስተፅኦ በማድረግ መልኩ የገንዘብ አቅማቸውን ለማዳበር የሚያስችል ትርፍ ውሃ ስለመኖሩ ማጤን ፤
4. ያላቸው የውሃ ተቋም ትልቅነት( ለምሳሌ፡-ባለሞተር ጥልቅ ጉድጓድ በውሃ መሳቢያ ወይም በግራቪቲ የሚሰራ የተጠለፈ ውሃ ወይም ምንጭ) በራሳቸው እንዲቆሙ የሚያስችል የገንዘብ፤ የአስተዳደርና የቴክኒክ አካላት እንዲኖሯቸው የሚፈቅድ ነው ወይስ ትናንሽ ተቋማትን(ትልቅ ያልሆኑና በእጅ የተቆፈሩ)ወይም በቦታቸው የለሙ ምንጮችን ብቻ ያቀፈ ስለመሆኑ መለየት፤
5. በራሳቸው ገንዘብ ከገለ ክፍለ ኢኮኖሚ ሊገዙ የሚችሉት የመለዋወጫና የጥገና አገልግሎት እንዴት ሊያኙ እንደሚችሉ እና መለዋወጫዎችን በግዥ ለማቅረብ የሚያስችል ተዘዋዋሪ(ሮቮልቪንግ)ፈንድ( በማንም የተደራጀ ይሁን)ስለመኖሩ ማረጋገጥ፤
6. በራሳቸው የጥገና ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል አቅም ከሌላቸው በምን መልኩ አቅማቸውን ሊያጎለብቱ እንደሚችሉ መለየትና ማስቀመጥ፤
7. የራሳቸውን የተሟላ ጽ/ቤት ለማቋቋምና እንዲሁም ስራ አስኪያጅና ሌሎች ሰራተኞች ለመቅጠር የሚያስችል ግዙፍነትና የገንዘብ አቅም ስለመኖራቸው፤
8. በአንድ አቅራቢ የተለያዩ የውኃ ተቋማት ካሉ የተቋማቱ የስብጥሩ ተመጣጣኝነት ምን እንደሚመስል በማየት እና እንደየ ሁኔታው በየትኛው ደረጃ(ጎጥ፤ሰፈራ፤መንደር፤ንዑስ ቀበሌ ወይም ቀበሌ ወዘተ.) አደረጃጀቱ ተመራጭነት እንዳለው መለየትና ጥቅምና ጉዳቱን በመለየት ለተጠቃሚው ፈቃደኝነት ላይ በመመርኮዝ ማስተካከል፤
9. ተቋማቱ ዘላቂነት ባለው መንገድ እንዲጓዙ ለማድረግ መጀመሪያ ላይ ምን አይነት አቅም ግንባታና የቴክኒክ እርዳታ እንዲሚያስፈልግ በመለየት ምን አይነት መዋቅር፡ቢሮና ሰራተኞች እንደሚያስፈልጉ መለየት፤
10. መቀናጀት የሚያስፈልጋቸው የጋራ ጉዳዮችን በመለየት ለቅንጅታዊ አሰራር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፤

## 7.በአንድ ማኅበር/የውኃ ተቋም/ ብቻ ለማከናወን ስለሚያስቸግሩ ተግባሮች እና በጠቅላላ ጉባኤ ሊፈቱ የሚገባቸው ጉዳዮች፤

ከላይ በአንቀጽ 6 ስር ያሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በእያንዳንዱ ተቋም ብቻ ለማከናወን አስቸጋሪ የሆኑ አገልግሎቶች ፣ ከዚህ በታች በተጠቀሱት በተዘረዘረው መልኩ በጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፤

1. የኦፐሬሽንና ጥገና እንዲሁም ሌሎች የተቋም አስተዳደር መመሪያዎችንና ጥራዞችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት ተግባራትን ስርአታዊ በሆነ አኳኃን ለማከናወን የሚያስችሉ አካሄዶችን በስራ ላይ ማዋል፤
2. ተቋሙን በማካሄድ ስራ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችንና ሰራተኞችን አቅም ለመገንባታ በታቀደ መልክ እንደአስፈላጊነቱ የስልጠና ፕሮግራም ፣ቢዝነስ ፕላን ጨምሮ ማዘጋጀትና ማካሄድ ፤
3. ለተቋማት ማስፋፊያ ወይም እድሳት የሚውል ገንዘብ ከውጭም ከአገር ውስጥ ምንጮች መፈለግ ፣ማግኘትና ውጭ ማድረግ ፤
4. ከሃገር ውስጥ ገበያ ወይም ከውጭ ገቢ በማድረግም ይሁን የመለዋወጫ ዕቃዎችንና ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውሃ ማከሚያ ኬሚካሎች ወዘተ በጅምላ በመግዛት ዋጋቸውን የቀነሰ እንዲሆን ፤
5. የተለያዩ ታሪፎችን እና ክፍያዎችን በመወሰንና በመከለስ ረገድ አባል ተቋማትን መርዳት፤
6. የቴክኒክ ምክር ለማግኘትና ለመጠቀም አቅም መፍጠር፡፡

# ክፍል ሦስት

## ስለ ውኃ ተቋማት ተጠቃሚነት መመዘኛ ፤ የአባልነት መስፈርት፤ መብቶችና ግዴታዎች

### 8.የውኃ ተቋማት ተጠቃሚነት አወሳሰን

የውኃ ተቋማት ተጠቃሚ ህብረተሰብ ተብለው የሚሰየሙ ሰዎች ወይም ቤተሰቦች ቁጥርና ተጠቃሚነት የሚወሰነው ተቋሙ በሚሰጠው የውኃ መጠን፣ የግለሰብ ወይም የቤተሰብ ፍጆታ አሰፋፈር ጥቅጥቅነት እንዲሁም ቤተሰቦች ከውኃ ተቋሙ ያላቸውን ርቀት መሰረት አድርጎ የሆናል ፡፡ የሚመለከተው የውሃ ቢሮ ወይም ጽ/ቤት ከቀበሌ አስተዳደሮችና ከማህበረሰቦቹ ጋር በመማከር ተጠቃሚ ህ/ሰብ በሚያመቸው አኳሃን ተደልድሎ አገልግሎት እንዲያገኙ ይወሰናል ፡፡

### 9.የአባልነት መስፈርቶች

1. የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች በማህበራቱ አገልግሎቶች ለመጠቀም የፆታ ፣የማህበራዊ ፣የዘር፣የፖለቲካ፣ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ፣ የአባልነት ግዴታዎችን ለመወጣት ለሚችሉ ሰዎች በሙሉ ክፍት ሆኖ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች ናቸው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ስር ያለው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ካሟላ ማንኛውም ሰው የማህበሩ አባል ለመሆን ይችላል ፡፡

ሀ) አስራ ስምንት ወይም ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው ፤

ለ) ማህበሩ ስራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ ውስጥ ከሆኑ፤

ሐ) በማህበሩ የሚወሰነውን የመመዝገቢያ ክፍያ መፈጸም የሚችል፤

መ) እንደ ማህበር አባልነታቸው የሚጠበቅባቸውን ግዴታዎች ለማክበር ፈቃደኛ የሆኑ፤

ሠ) አረጋውያን ፣ አካል ጉዳተኞችና ከዕድሜ ጋር በተያያዘ መልኩ የደከሙ የአካባቢው ነዋሪዎች እነደ አስፈላጊነቱ በቀበሌ አስተዳደር ሲረጋገጥ እና ሲወሰን በቀጥታ ያለምንም ክፍያ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ረ) ከላይ በ"ሠ" ስር በተደነገገው መሰረት ተጠቃሚ የሚሆኑ ነዋሪዎችን ግዴታ የቀበሌው አስተዳደር ይወጣል ፡፡

## 10. የማኅበሩ አባላት መብቶች

1. በማኅበሩ የሚወሰነውን ክፍያ በመክፈል ከሚመለከታቸው ተቋማት የመጠጥ ውሃ መውሰድ፤

2. እንደ አግባብነቱ በማህበሩ ስብሰባዎችና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች በንቃት መሳተፍ ፤

3. ከሁሉም ሌሎች አባላት ጋር በመሆን የራሳቸውን የመመረጥ መብት ጨምሮ በምርጫ ሂደት ውስጥ እኩል የመሳተፍ ዕድል፤

4. በራሳቸው ተነሳሽነት ከአባልነት መሰናበት፤

## 11. የማህበሩ የአባላት ግዴታዎች

1. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰኑት ውሳኔዎች ማክበር ፤

2. በማህበሩ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ወይም ጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ስራዎች ወይም ተግባራት አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ መሳተፍ፤

3. የማህበሩ የሆኑ ንብረቶችን፣ማሽነሪዎች ፣ መሳሪያዎችን እና ማህበሩ የሚጠቀምባቸውን ሌሎች ሀብቶች በሚመለከት የተሟላና ተገቢ እንክብካቤ ማድረግ፤

4. በማህበሩ ለተሰጡ አግልግሎቶች እና ለኦፕሬሽንና ጥገና የሚደረጉ ወጭዎችን ለመሸፈን በየጊዜው በማህበሩ ጠቅላላ ስብሰባ የሚወሰኑ ክፍያዎች የሚመለከቱ የፋይናንስ ግዴታዎችን በሙሉ በወቅቱ መፈፀም፤

5. በማህበሩ የውሃና ሳንቲሽን ኮሚቴ /ጥሪ በሚደረግላቸው ጊዜ በውሃ ተቋሙ ጥገና ስራ መሳተፍ፤

6. የውኃ ተቋማቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሚደረጉ አጠቃላይ ጥረቶችና ተግባራት ውስጥ የውሃ ተቋማት አካላት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን የመተግበር፤

## ክፍል አራት

## 12.ስለ ማህበራቱ አካላት በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 12 ሥር በተደነገገው መሰረት፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ ፤
2. ሥራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ
3. አስፈላጊ ሰራተኞች ይሆናሉ፡፡

## 13. የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 14 በተደነገገው መሰረት ይሆናል ፡፡

## 14.ሥራ አስፈጻሚ የውኃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የሥራ አስፈጻሚ የውኃና ሳንቴሽን ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 16 መሰረት ይሆናል ፡፡

## 15.ስለጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

ሀ) የውስጥ ደንቡ ጸድቆ ማህበሩ ከተመዘገበ በኋላ የማህበሩ የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ በጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪ ይሰበሰባል ፡፡

ለ) ከላይ በንዑስ 1 ስር የተጠራው ስብሰባ የማህበሩ ሹመኞች/ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት/የሚመረጡበትና የስራ ክፍፍልና ርክክብ የሚደረግበት ስብሰባ ነው ፡፡

ሐ) ከላይ በንዑስ 2 ስር በተጠቀሰው መሰረት በተደረገው የስራ ክፍፍልና ርክክብ መሰረት ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ስራ ይጀምራል፡፡

## 16.የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባና ስነ-ስርአት

1. ጠቅላላ ጉባኤው በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 14 ስር የተሰጡትን ተግባራት ለመፈጸም በዓመት ቢያንስ 2 ጊዜ ይሰበሰባል፤ እንደ አስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይቻላል ፡፡

2. የጠቅላላ ጉባኤው ምልዐተ ጉባኤ ከግማሽ በላይ አባላት የተገኙበት ይሆናል፤

3. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1-3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዝርዝር የስብሰባ ስነ-ስርዓት የአጀንዳ አቀራረብና አወሳሰን ወደ ፊት በሚወጣው መመሪያ ወይም በማህበራቱ የውስጠ ደንብ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

## 17.ስለ ጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ

1. የውሃ ተቋሙ ህልውና አደጋ ላይ መውደቁ ሲታመንና በማህበሩ አባላትም ሆነ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ፤

2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነቱ በተሟላ መልኩ መወጣት ሲያቅተው፤

3. በውኃ ተቋሙ ዙሪያ ላይ ግድፈትና የከፋ አሰራር ሲኖርና በአባላት 1/3ኛ ጥያቄ ከቀረበ ፤

4. የውሃ ተቋሙ ህልውና አደጋ ላይ ሲሆንና ልዩ ውሳኔ ለመወሰን የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ ይህም በስራ አስፈጻሚው የውሃ ሳንቴሽን ኮሚቴ ሲታመን ፤

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1-4 ስር የተቀመጡ ነጥቦች ሲሟሉ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

## 18. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ አመራረጥ ተግባርና ኃላፊነት

1. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚሆኑት በማህበሩ ጠቅላይ ጉባኤ ከሚመረጡ የውሃ ንጽህናና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ የተመረጠው ሰው ይሆናል፡፡

2. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢው ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤውና ለውሃ ንፅህናና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ነው፡፡

3. ሰብሳቢው የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል ፡፡

ሀ/ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን በዚህ ደንብና በማህበሩ ህገ ደንብ መሰረት መጥራትና መምራት፤

ለ/ ከጽሐፊውና ከስራ አስፈጻሚው የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ አማካኝነት ከጠቅላላ ጉባኤ ቀን በፊት ቀደም ብሎ አጀንዳዎችን መቅረጽ፤

ሐ/ በስራ አስፈጻሚው የውሃ ሳኒቴሽንና በጠቅላላ ጉባኤው የሚወሰኑ ውሳኔዎችን የማስፈጸምና ተገቢውን የስራ ሪፖርት ማቅረብ፡፡

መ/ በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ማህበሩን ይወክላል፡፡

## 19. ስለጸኃፊ ተግባርና ኃላፊነት

የነጠላ ማህበራቱ የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጸሀፊ የጠቅላላ ጉባኤ ፀሀፊ ሲሆን ከአንድ በላይ የሆነ ማህበራት የሚመሰርቱት ልዕለ ማህበር ከሆነ ከሁሉ ስራ አስፈጻሚ የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ ፀሀፊዎች መካከል በድምጽ አብላጫ ድምጽ የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ከሰብሳቢው ጋር በመሆን አጀንዳ መቅረጽ፤ ቃለ ጉባኤ እና ሌሎች የማህበሩን ሰነዶች በሚገባ መያዝ፡፡
2. ሰብሳቢው በማይገኝበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፡፡
3. በሰብሳቢው ተለይቶ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡
4. የተለያዩ የስብሰባ ጥሪዎችን ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ማዘጋጀትና ማሰናዳት፤

## 20 ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አመራረጥ ሁኔታ

1. የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡና ተጠሪነታቸውም ለዚሁ ጠቅላላ ጉባኤ ብቻ የሆኑ የውሃና ንጽህና/ሳኒቴሽን ኮሚቴዎች ይኖሯቸዋል፡፡
2. የውሃና ንፅህና/ሳኒቴሽን ኮሚቴዎች የሚመረጡበት ከማህበሩ አባላት መካከል ብቻ ነው
3. የውሃና ንፅህና/ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት ቁጥር በማህበራቱ መተዳደርያ ደንብ የሚወሰን ሲሆን ከሰባት አባላት በታች ሊሆን ግን አይችልም፡፡ ከነዚህ መካከል አብዛኞቹ ሴቶች እንዲሆኑ ይደረጋል ፡፡
4. የምርጫ መመዘኛዎች ችሎታና የስራ ውጤት/መጣኝነት(ሜሪት)ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ
5. የውሃ ንጽህና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት የአገልግት ዘመን ሶስት አመት ይሆናል፡፡
6. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው ቢኖርም ፣ ለ35 በመቶ የኮሚቴዎች አባላት የመጀመሪያ ጊዜ የአገልግሎት ዘመን አራት አመት ይሆናል፡፡ ይህም በአንድ ጊዜ የቆዩ አባላት በሙሉ በአዲስ አባላት እንዳይተኩ ለማድረግ ነው፡፡

7. በወቅቱ ተገኝተው ድምጽ ከሚሰጡን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው አባላቱ እንደገና እንደሚመረጡ ድጋፍ ካልሰጡ በስተቀር የውሃና ንጽህና/ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሊመረጡ አይችሉም፡፡
8. የውሃና ንፅህና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት በማንኛውም ምክንያት ስራቸውን ሲለቁ በስራ ዘመናቸው የተፈፀሙ ተግባራት እንዲመረመሩ (ኢንስፔክት እንዲደረጉ)የማስደረግ ግዴታ አለባቸው ፡፡
9. ለውሃና ንፅህና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ውሳኔዎች የሚያስፈልገው ምልዐተ ጉባኤ ከኮሚቴው አባላት ሁለት ሶስተኛ ያነሰ መሆን የለበትም፡፡
10. የቀበሌው የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ የመንግስት ተቃማት ተወካዮች (የጤና ፤ የውሃ፤የግብርናና ሌሎች ባለሙያዎች እንዳስፈላጊነቱ የኮሚቴ አባል ይሆናሉ፡፡
11. ስራ አስፈፃሚው የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ ለውሃ ተቋሙ ዘላቂነት እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ቴክኒካዊ ንዑሳን ኮሚቴዎች ማለትም የጥገና ፤የግዥ ፤የንጽህና ፤ የጥበቃ… ወዘተ ሊያቋቁም ይችላል ፡፡ዝርዝሩ ወደፊት ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው ዝርዝር የአፈፃጸም መመሪያ የሚገለጽ ይሆናል፡፡

## 21. ስለ ውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ ሰብሳቢ እና ፀሃፊ አመራረጥ

1. የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ ሰብሳቢ በኮሚቴው አብላጫ ድምፅ ይመረጣል
2. ሰብሳቢው ከውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት ውስጥ ፀሃፊውን ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል

## 22. የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር፤

የሌሎቹ ውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አመራር(ሂሳብ ሹም ፤ገንዘብ ያዥ ፤ቁጥጥር ፤አባላት …ወዘተ) ዝርዝር ስልጣን እና ተግባራት አሉት ፡፡

1. የማህበሩ አጠቃላይ አመታዊ እቅድ ዝግጅትን ይመራል ፤
2. በጠቅላላ ጉባኤና በውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በበላይነት ያስፈጽማል ፡፡
3. የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባዎችን ይመራል ፡፡
4. ማንኛውንም የማህበሩን ዕቅድ ፕሮግራም ያስፈፅማል ፤
5. ለሚመለከተው አካላት ሪፖርተሮችን ያቀርባሉ ፤
6. በሶስተኛው ወገኞች ዘንድ ማህበሩን ይወክላል ፤

## 23. የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ አመራር ከሃላፊነት ስለሚነሳበት ሁኔታ

1. ተግባርና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ሳይችሉ ሲቀሩ፡፡ይኸውም

ሀ. አካባቢ ለቀው ሲሄዱ
ለ. በህመም ወይም በአቅም ማነስ ምክንያት ኃላፊነቱን መወጣት አይችልም ተብሎ ሲታመን ፤

2. ሙስናን ጨምሮ ከስነምግባር ብልሹ አሰራር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የአሰራር ግድፈቶች ሲገኙና ሲረጋገጡ

## 24. የአደረጃጀትና የአወቃቀር አማራጮች

1. የመጀመርያ ደረጃ ማህበራት የሚሆኑበት ጊዜ ሁሉም የማህበሩ አባላት የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሲሆኑ ስራ አስፈፃሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ/ቦርድ አባላት በሙሉ በጠቅላላ ጉባኤ አባላት በቀጥታ ያለውክልና ይመረጣሉ፡፡

2.የሁለተኛ ደረጃ ማህበራት በሚሆኑበት ጊዜ የእያንዳንዱ ማህበራት ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት የሁለተኛ ደረጃ ማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ይሆናሉ ፡፡

3.በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀፅ 27 መሰረት የሚቋቋሙ የሁለተኛ ደረጃ ማኀበሩ ስራ አስፈጻሚ የውሃ ሳኒቴሽን ኮሚቴ አባላት የሚሆኑት የእያንዳንዱ ማሕበር ሰብሳቢ እንደ አስፈላጊነቱ ሌላ አንድ አንድ ተጨማሪ የኮሚቴ አባላት ይሆናሉ ፡፡

## 25. ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ስብሰባ ስነ ስርዓት ሁኔታ

1.የስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ በአዋጅ ቁጥር 71/2000 አንቀጽ 16 የተጣለበት ኃላፊነት ለመወጣት ፡

ሀ- ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል ፤

ለ-ምልዓተ ጉባኤው የሚሟላው ከግማሽ በላይ አባላት ሲገኙ ነው፡፡
ሐ-የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙት ሁለት ሶስተኛ ድምጽ ይወሰናል ፡፡

# ክፍል አምስት

# የመንግስት እና የሌሎች አካላት ሚና

## 26. የተቆጣጣሪው አካል ተግባርና ኃላፊነት

የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር በአዋጅ ቁጥር 71/2000 እና በዚህ ደንብ የተሰጡትን አላማዎች ወደ ግብ ለማድረስ የተቆጣጣሪው አካል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት

1. ተገቢ ስልቶች በማዘጋጀት እና ህጎችን ደንቦችና መመሪያዎችን ማሟላት የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ አቅርቦትን የሚመለከቱት የብሄራዊ ፖሊሲው ክፍሎች ባግባቡና አመርቂ በሆነ መልኩ መተግበራቸውን ማረጋገጥን፤
2. ከብዙ በጥቂቱ የውሃ ጥራት ቁጥጥርን፤ የታሪፍ አወሳሰንና አከላለስ ዘዴዎችን፤ የገንዘብ ጉዳዮች ክትትልና የኦዲት ተግባራትን በሚመለከት መመሪያዎችን በማዘጋጀት ማውረድና የክትትል ተግባራት በሚመለከት መመሪያዎችን በማዘጋጀት ማውረድና የክትትል ተግባራትን ማከናወን ፤
3. የመረጃ ስርአት አስተዳደርን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግን ፤
4. የአዋጁን ድንጋጌዎች አፈጻጸም፣በተለይም የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተቋማት አስተዳደር በሚመለከት በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ የውሃ ጽ/ቤቶች ፣ሰራተኞቻቸውና ሌሎቸች ባለድርሻዎች የሚሆን የአቅም ግንባታ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ፣
5. በአጠቃላይ የዐዋጁን የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አፈጻጸም የሚመለከት ክትትልና ግምገማ ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማድረግን፣ በጥናት ላይ በመመስረት የተሻሉ አሰራሮችን ማዳበርና ተግባራዊ ማድረግ፤
6. በተጠቃሚ ማህበረሰቦች ፣ የውሃ ክፍለ ኢኮኖሚ አካላት ፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች አግባብ ያላቸው የሲቪል ማህበረሰብ አካላት መካከል ሽርክና የሚመሰረትበት ሁኔታ ማመቻቸትን፤
7. የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ ማበረታታትን የመለዋወጫ አቅርቦትን ፣የጥገና አገልግሎትንና ተቋማትበማስፋፋት የውሃ ተቃሙ እና ማህበራቱ እንዲጠናከሩ መርዳት፡፡
8. ሌሎች የውሃ ተቋማትን ፤ማህበራትንና የወረዳ ውሃ ማዕድንና ኢነርጂ መስሪያ ቤቶችን የሚያጠናክሩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

## 27. የወረዳ ውሃ ማዕድንና እና ኢነርጂ ጽህፈት ቤት ሃላፊነት

በዚህ ደንብ መሰረት የሚቋቋሙትን የውሃ ማህበራት የሚፈለግባቸው ውጤት ለማስገኘት እንዲችሉ የወረዳው ውሃ ማእድን ኢነርጂ ጽ/ቤቶች የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች አሉት፤

1. ማህበራትን ማደራጀትና በሂደት ከክልል ውሃ ማ/ኢ/ህ/ል ቢሮ በሚሰጣቸው ውክልና መሰረት መመዝገብን ፣

2. በክልሉ መንግስት በሚወጡ አዋጆች ደንቦችና መመርያዎች እንዲሁም በውስጥ ደንባቸው መሰረት ማህበራትን ለመምራትና የውሃ ተቋማትን ለማካሄድ የሚያስችል ልዩ ትኩረት ያለው ስልጠናና ሌሎችም እርዳታዎች መስጠት፤
3. ጥገናን የመሳሰሉ ቴክኒክ አገልግሎቶች ለገጥር የቤት ውስጥ አገልግሎት ውሃ ተቋማት በክፍያ መስጠት፡፡ የዚህ አይነት አቅም እስኪፈጠር ድረስ ከዞኖች ከቢሮዎች ድጋፍ የሚገኝበት የመሸጋገርያ ጊዜን በመጠቀም ክፍተቶችን መሙላት፡፡
4. አገልግሎቶች በሌሎች እንዲሰጡ የሚደረጉ የውል ሁኔታዎችንና በአጠቃላይ የኮንትራት አስተዳደርን በመሳሰሉት ተግባራት አካባቢ የቴክኒክ ድጋፍና ስልጠና እንዲሁም ምክር መስጠት፤
5. ተቋማቱ ከዐቅም በላይ ሆኖ ሲገኝና ተቋማቱ ራሳቸው ሲጠይቁ የውሃ ቆጣሪዎች ፣የውሃ መሳቢያዎች ፣ጄኔረተሮች ወዘተ ለተቋማቱ መግዛት፤
6. የውሃ ጥራት ቁጥጥርን፣ታሪፎች ቀድሞ በተሰጠ የአወሳሰን መመሪያ መሰረት መሆናቸውን ፣ጠቅላላ ስብሰባዎች በየጊዜው መካሄዳቸውን እንዲሁም የኦዲት ተግባራትን በሚመለከት በተቋሞቹ ላይ የቁጥጥር ስራዎች ማከናወንን፡፡
7. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑና የውሃ ተቋማትና ለማህበራቱ ጠቃሚ የሆኑ የእገዛ ተግባራት ይወጣሉ፡፡

## 28. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር አካላት ሚና

እንደ አግባብነቱ የወረዳ እና ቀበሌ አስተዳደር አመራር የገጠር የቤት ውስጥ አገልግሎት የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት መመስረትም ሆነ ከተመሰረቱ በኃላ ለውጤታማነታቸው የሚግዙትን ማናቸውንም ተግባራት የመፈጸም ኃላፊነት የሚኖራቸው ሲሆን በተለይም ህዝብን በማወያየት ፣በማሳመን በማነቃነቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

## 29. የሌሎች ባለድርሻ(ተባባሪ) አካላት ሚና

የውሃ ተቋማት ማኅበራትን ለማደራጀትና ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፤ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የየራሰቸው ድርሻ የሚኖራቸው ሲሆን በተለይም የእርዳታ ሰጪ ተቋማትን ድጋፍ ለማበረታታትና ለማጠናከር ዝርዝር አፈጻጸም ተቆጣጣሪው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል ፡፡

# ክፍል ስድስት

## ስለ ማህበራት የውስጥ ደንብ ፣አቋም ፣ህልውናና መፍረስ

## 30.ስለ ማኀበሩ የውስጥ ደንብ

1.እያንዳንዱ ማህበራት የየራሳቸው የመተዳደሪያ ውስጠ ደንብ ይኖራቸዋል

2. ከላይ በንዑስ 1 ስር የሚኖረው የውስጥ ደንብ የሚከተሉት ይዘቶች ይኖረዋል፡፡

ሀ) የማህበሩና ስምና አድራሻ፣

ለ)የማህበሩ ዓላማና ተግባራት

ሐ)የማህበሩ አባል ለመሆን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች

መ) የአባላት መብቶችና ግዴታዎች ፣

ሠ) የማህበሩ ስራ አመራር አካላት አመራራጥ፣ስልጣንና ተግባርና ፣ እና ዝርዝር የስብሰባ ስነ ስርአት

ረ) ከማህበሩ አባልነት ለመልቀቅ እና ለማሰናበት (ለመባረር) የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሰ) ለመመረጥ ፣ለመሾም የሚያበቁ ሁኔታዎች ፣ያገልግሎት ዘመን ፣የማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት የሚሰናበቱበት(የሚባረሩበት) ሁኔታዎች፣

ሸ) ስብሰባ ለመጥራት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችና የድምጽ አሰጣጥ ስርዐቶች ፣

ቀ) ሰራተኞች ስለሚቀጠሩበት እና ኦዲት ስለሚካሄድበት ሁኔታ፤

በ) ከአዋጁ ፤ደንብና ህጎች ጋር የሚቃረኑ ሌሎች ሃሳቦችን ያካተተ ይሆናል

3. የውስጠ ደንቦች ለዚሁ ተብሎ በሚጠራ የተጠቃሚዎች ስብሰባ (በጠቅላላ ጉባኤ በአብላጫ ድምጽ)መጽደቅ አለባቸው፡፡

## 31. ስለ ማህበራቱ አቋምና ህልውና

በአዋጅ ቁጥር 71/2000 እና በዚህ ደንብ መሰረት የሚቋቋሙ የውሃ ተቋማት ማህበራት ህጋዊ ሰውነት አላቸው፡፡

## 32. ስለ ማህበሩ መፍረስ

1.አባላቱ ማህበሩ እንዲፈርስ ልዩ ውሳኔ ሲያስተላልፉ፣

2. የውሃ ተቋማት አገልግሎት ሙሉ በሙሉ በዘላቂነት ሲቋረጥ

3. የአባለት ቁትር ከ10 በታች ሲሆንና ተቆጣታሪዉ አካል እንዲፈር4ስ ወሳኔ ሲያስተላልፍ፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፣ የመፍረስ ዉሳኔ የተላለፈበት ማህበር እንዲህ ዓይነት ወሳኔ የተላለፈበት ስለመሆኑ ዉሳኔዉ በተላለፈ በ7 ቀናት ዉስጥ የተቆጣጣሪዉ አካል ያሳዉቃል ፡፡

## ክፍል ሰባት
## የዉሃ ተጠቃሚ ማህበራት የገንዘብ ምንጭ፣
## መዛግብት አያያዝና ሂሳብ ነክ ጉዳዬች

## 33. የዉሃ ተጠቃሚ ማህበራት የገንዘብ ምንጭ፣

1. የማህበሩ ገንዘቦች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምንጮች ይሆናሉ፡-

ሀ/ ከዉሃ ሽያጭና እንዲሁም ቧንቧ ከማስቀጠልና ከሌሎች የተያያዙ ስራዎች የሚገኝ ገቢ፣

ለ/ ንብረት ከመሸጥ የሚገኝ ገቢ፣

ሐ/ በጠቅላላዉ ጉባዔ ዉሳኔ መሰረት በአባላት የሚደረጉ መዋጮዎች፣

መ/ ምግባር ሰናይ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ከመሳሰሉ የተለያዩ ሌሎች አካላት በጥሬ

ገንዘብ ወይም በአይነት የሚደረጉ መዋጮች፡፡

2. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የማህበሩ ገቢዎች እንደ ቅደም ተከተላቸዉ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጉዳዬች ብቻ እንዲዉሉ ያደርጋል፡-

ሀ/ የኦፐሬሽንና ጥገና ወጭዎችን በሙሉ ለመሸፈን፤

ለ/ የተሃድሶ ወይም የመስፋፋት ስራዎችን ለማከናወን፤

ሐ/ የህዝብ መፀዳጃ አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፤

መ/ በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚፀድቀዉ መሰረት ተጠቃሚዉ ማህበረተሰብ የሚያስፈልጉትን ሌሎች የልማት ፍላጎቶች ለሟሟላት ፡፡

## 34. የማህበሩ ሀብቶች የማይከፈሉ ስለመሆኑ

የማህበሩ ሀብቶች በአባላቱም መካከል ሆነ ወይም በሌላ በማንኛዉም ወገን በነፍስ ወከፍ ሊከፋፈል አይችልም ፡፡

የማህበሩ ህልዉና እንዳለ በተለያዩ ምክንያቶች ከአባልነት የሚወጡ አባላት የድርሻቸዉን ንብረት መጠየቅ አይችሉም፤

## 35. የሂሳብ መዛግብቶችና ዓመታዊ ሪፖርቶች

1. የማህበራት ሂሳብ አያያዝና አጠቃቀም ህጋዊ አግባብነት የተከተለ ሆኖ ተቆጣጣሪው አካል ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚያወጣው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

2. አጠቃላይ የማህበራት ዕቅድና አፈጻጸምን በተመለከተ ስራ አስፈጻሚ የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ደረጃውን የጠበቀና ዝርዝር ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ማቅረብ አለበት፡፡

## 36. የሂሳብ ዓመት

የማህበራቱ የሂሳብ ዓመት የክልሉ የሂሳብ ዓመት ይሆናል፡፡

## 37. ኦዲትና ኢንስፔክሽን

1. ተቆጣጣሪው አካል ወይም በዚሁ አካል የተሰየመ ሌላ አካል ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ የሂሳብ ዓመቱ በተጠናቀቀ በሶስት ወራት ውስጥ በዚህ ዐዋጅ መሰረት የተቋቋሙ ማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፡፡
2. የኦዲት ዘገባው ለተቅላላው ጉባኤና ለተቆጣጣሪው አካል ይቀርባል፡፡
3. በተጨማሪም ተቆጣጣሪው አካል በማናቸው ጊዜ የማህበራቱን የስራ አፈጻጸም፣ ሰነዶችን እና የፋይናንስ አቋም በሚመለከት ድንገተኛ ኢንስፔክሽን ራሱ ማካሄድ ወይም በሌሎች በሚወክላቸው አካላት አማካኝነት ማካሄድ ይቻላል፡፡
4. የንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 ድንጋጌዎች እንድተጠበቁ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ደግሞ ኢንስፔክሽን ሊካሄድ ይችላል፣
   ሀ) የውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴው አብዛኛው አባላት ጥያቄ ሲያቀርቡ ፣
   ለ) ከጠቅላላው የማህበር አባላት አንድ ሦስተኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት እንዲህ
   አይነቱ ኢንስፔክሽን እንዲካሄድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፡፡

## 38. የሂሳብ አጣሪዎች

ተቆጣጣሪው አካል ከውሃና ሳኒቴሽን ኮሚቴ ወይም ከጠቅላላ ስብሰባ ማመልከቻ ሲቀርብለት ሂሳብ አጣሪ ይሰየማል፡፡የሂሳብ አጣሪዎች ስልጣንና ተግባር በፍትሐብሄር ህግ አንቀጽ 459 እስከ 467 በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

# ክፍል ስምነት

# ልዩ ልዩ ደንጋጌዎች

39. መመሪያ ስለማውጣት

በዚህ ደንብ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ ለአፈጻጸም ያመች ዘንድ ተቆጣጣሪው አካል ዝርዝር መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አለው፡፡

40. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብና መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም

41. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ፀድቆ ከወጣበት ቀን ---------------------- 2005ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር